# <<በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውኃ ይጠጣል!>>


ከቢታገሡ በላቸው

ካሊፎርኒያ

ዩስኤ (USA)


.........................................................

በአራት ኪሎ በማርካቶ፤
ቦምብ እና ድንጋይ ተዘርቶ፤
ተባለና አገር ለምቶ፤
ቁም-ነገር ተገኝቶ የሀገር ፍቅር ተወርቶ፤
የአገር ግንባታ ባሕረ-ሐሳብ ተገብቶ፤
ግን ምን ይደረግ ሰላማዊው ትግል ዋናው ተረስቶ፤
የሕዝቦች ትግልና ቁጣ ማዕበል ተነስቶ፤
የአንዱን መብት ሲከበር የሌላው ግን ቀርቶ፤
አይሆንም፣ ይህማ አይሆንም! ...አያዋጣም ከቶ፤
ውኃ መሆን ነው በውኃ ተበልቶ።

...........................................................................

የካ. ፲፮/፲፱፻፺፰ ዓ/ም

## *በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውኃ ይጠጣል!*

*ከቢታገሡ በላቸው*
*ካሊፎርኒያ*

*ለሕዝቦች እኩልነት፤*
*ለተረጋጋ ሕይወት፤*
*ፍትሕ …ርትዕ ለነገሰባት፤*
*ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት፤*
*ኢትዮያን ለመመሥረት፤*
*ለመሆን የሕይወት መስዋዕት፤*
*ለተበጀችሁ ታጋይ አእላፍ ሰማዕታት፤*
*ለክሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት።*

*አሜን! አሜን! ወአሜን በሉ፤*
*ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በሙሉ፤*
*ስብሐት ወክብር ኵለሄ ይደሉ።*

*ስለዚህ ሰላምታ ብቻ ሳይሆን፤*
*ክብር ወዝክር ለእናንተ ይሁን፤ ….አሜን!!!*

<<ትዕግሥት መራራ ናት፣ ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው>> የተባለውን ነገር እውን ለማድረግ የኢትዮጵያ ታጋይ ሕዝቦች ያሳያችሁት ትዕግሥት እና የትዕግሥት የመጨረሻ ውጤት የሆነችው ጣፋጯ ፍሬ-ሰላምን ለማስገኘት እየከፈላችሁት ያለው መስዋዕት ሁሉ በጣም አስደናቂ ነው። ድንጋይና ቦምብ እየተወረወረባችሁ እስከ ሞት ድረስ በመታገሳችሁ መስዋዕትነታችሁ ልክ ከይሳቅ ትዕግስትና መስዋዕት ጋር አመሳስሎታል። ይሳቅ አባቱ አብርሃም እሱን አርዶ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ለማቅረብ በግዐ-መስዋዕት አድርጎ ሲያዘጋጀው ይሳቅ መስዋዕት ለመሆን ምንም አላመነታም። እንዲያውም ይሳቅ የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀምና ለፈጣሪው መስዋዕት እንዲሆን በመመረጡ ሳይደሰት አልቀረም። ምክንያቱም ይሳቅ የመስዋዕት እና የሞት ልዩነት ጠንቅቆ የተረዳ ቅዱስ ሰው ነበር። ከዚህ ባልተለየ መልኩ እናንተም ለኢትዮጵያ የሕግ መኖርና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ስትሉ፣ ለዜጎች ሁሉ የዲሞክራሲ መብቶች፡- ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴና የእምነት ወይም የአምልኮ ነጻነትን ለማረጋገጥ ቤዛ ሕዝብ ሆናቹኋል፤ የሕዝቦች እኩልነት፡- የፆታ፣ የዕድሜ፣ የነገድ፣ ወይም የብሔር እና ብሔረ-ሰብ ልዩነትና አድልዎ የሌለባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ግንባር ቀደም በመሰለፍ ተሰውታችኋል። ስለዚህ ለዘመናችን ሰማዕታት ጀግኖች ታጋይ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በድጋሚ ክብርና ምስጋና ይድረሳችሁ።

በተለይ በዘንድሮ የጥምቀት ክብረ-በዓል ላይ ረብሸኞች ባደረሱት በደል ምክንያት ኢትዮጵያውያን ሁላችን በያለንበት ድርጊቱ አሳዝኖናል፣ አስቆጥቶናልም። በእርግጥ ይህንን ወንጀል (**Crime**) የፈፀሙ ሰዎች ሰውን ማሳዘን እና ማስቆጣት ዓላማቸውና ተልእኳቸው ስለሆነ የፈፀሙት ረበሻና ግብረ-ሽበራ (**Act of terrorism**) አሳዝኖናል፣ አስቈጥቶናልም ስንል ይደሰቱ ይሆናል። ነገር ግን በዚህ የሚደሰቱ ከሆነ ሰዎቹ የሥነ አእሞሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። ወይም ደግሞ ፀረ-ኢትዮጵያ በሆነው የውጭ ኃይል ለሆዳቸው የተደለሉ ሆዳምና የሀገር ከሃዲዎች ናቸው። ከሁሉቱ አንዱ ወይም ሁሉቱ የእነሱ ችግር ነው። እኔ ግን በበኩሌ ስሜቴን ለመግለፅ <<በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውኃ ይጠጣል>> በሚል ርዕስ ይህችን ጽሑፍ አቀርባለሁ።

### በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውኃ ይጠጣል!

በዓለም ዙርያ በሁሉም ክፍላተ ዓለም ባሉት ሀገሮች የሚኖሩት ሕዝቦች ሁሉ የየራሳቸው ልዩ የሆኑት የእምነት ወይም የአምልኮ ሥርዓት፣ ባህል፣ ደንብ፣ ልማድና ቋንቋ ወዘተ. …አሏቸው። እነዚህ በየማኅበረ ሰቡ ማኅበራዊ ሕይወት (**Social life**) እንዲኖረው የሚያደርጉና እንደ ደም-ሥር የሚያገለግሉ የማኅበራዊ ሕይወት መጋቢዎች ናቸው። እነዚህ የሕዝቡ ጠቅላላ ታሪክ (**Total way of life**) የሚንፀባረቅባቸው ዋናዎቹ እምነትና ባህል

ነክ ጉዳዮች ናቸው ማለት ነው። የማንኛውም ሕዝብ እምነትና ባህል ነክ ጉዳይ ሁሉ መከበር ይገባዋል። ስለዚህ ይህነን ማክበር እና መውደድ ማለት ሕዝቡን ማክበርና መውደድ ማለት ነው፣ ይህነን ማቃለልና ማዋረድ ማለት ደግሞ ሕዝቡን መጥላትና ማዋረድ ማለት ነው።

በሕዝብ መቀለድ አይቻለምና እዚህ ላይ ሁሌ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። እምነትና ባህል ነክ ጉዳዮች ሁሉ የማኅበረ ሰብአዊ ሕይወት መሠረት ስለሆኑ፣ በዓለም አቀፋዊነት ወይም በሀገር አቀፍ ወይም በብሔር አቀፍ የሚከበሩበት ጊዜና ቦታን በማዘጋጀት ሕዝቦች በየሀገሮቻቸው ያከብሯቸዋል። የአከባበሩ ሁኔታም የሕዝቡ ማኅበራዊ የኑሮ ደረጃ፡- ሥልጣኔና ምጣኔ ሀብት በሚፈቅደው መሠረት በልዩ ልዩ መልክ ጉደናዎቻቸውና ዓውደ-ትዕይንቶቻቸውን ያስጌጣሉ። እንዲሁም ሕዝቦች በየአደባባዩ በነቂስ በመውጣት እየዘመሩ እና እየጨፈሩ በመንፈሳዊ ክብረ-በዓል መልኩ ወይም በብሔራዊ ሕዝባዊ ወኔ በኅብረት ያከብሩታል፣ ይደሰቱበታልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደ ሌሎች ሕዝቦች የራሱ የሆኑ ልዩ-ልዩ ሃይማኖታዊያን እና ሕዝባዊያን (ብሔራዊያን ወይም መንፈሳዊያን) በዓላት አሉት። ከእነዚህም አንዱ በየዓመቱ ጥር አሥራ-አንድ ቀን የሚከበረው የጥምቀት በዓል ነው። በዚህ መንፈሳዊ እና ባህላዊ ታላቅ ትዕይንት-ሕዝብ፣ ሕዝቦች ሁሉ አብረው ይደሰታሉ፣ ሆይ ይላሉ፣ ስሜታቸውን ይገልፃሉ። <<*ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ፣ ይበጣጠስ*>> በሚል ልበ-ሙሉነት እና ስሜት ሕዝባችን ያለውን ለብሶ እና አጊጦ ያከብረዋል። የጥምቀት በዓል አስደናቂ እና ልዩ የሚያደርገው፣ በዓሉ የሚከበረው የእግዚአብሔር ቃል--ታቦታተ ሕጉን ወደ የባሕሩ ወይም ወደ የወንዙ ይዘው በመሄድ የሚከናወን በመሆኑ ነው። ታቦታተ ሕጉ ባረፉበት ዙርያ ሁሉ ሕዝቡ ተሰብስቦ ይዘምራል፣ ሆይ ይላል፣ …ይጨፍራል፣ ዕልል …ዕልል ይላል፣ ይደሰታል። ነገር ግን የዛሬው ዓመት …የ፲፱፻፺፰ ዓ/ም የጥምቀት በዓል አከባበር <<*በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውኃ ይጠጣል*>> የሚያሰኝ ገጠመኝ ገጥሞታል። ይህ ጽሑፍም ይህንን መጥፎና አሳዛኝ ሁኔታ በተመለከተ ይሆናል።

ጥምቀት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሪነት በድምቀት የሚከበርበት ዋና ምክንያት ጌታችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቁ እንደ መታሰቢያ እና ታሪክ ሲሆን፣ በዋናነት ግን ጥምቀት ለክርስቲያኖች ለክርስትና ሕይወታችን መሠረቱ እሱ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ጥምቀት ሰውን እና እግዚአብሔርን ያገናኘ መንፈሳዊ ቃል-ኪዳን ነው። በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት እኛ ክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያን ስንባል ቃል-ኪዳኑ ትርጉም ሊኖረውና ሊፀና የሚችለው፣ በተግባር ክርስቲያን ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው። ይህ ማለትም ርአየ ሕቡአት (ልብና ኵላሊትን የሚፈትሽ ከሀሌ ኵሉ፣ ወጣኔ ኵሉ ወፈጻሜ ኵሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) ቅድመ ዓለም የነበረ፣ ያለ እና ለዘለዓለም የሚኖር ሕያው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ …እግዚአብሔር መሆኑን በእምነት በመቀበል፣ በጌታ ዘንድ ሁሉም ይቻላል በሚል የእምነት ኃይል፣ በተስፋ፣ በፍቅር፣ በትዕግሥት እና በመቻቻል አብረን ለመኖር ስንችል ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላካችን ሰላማዊ (የሰላም አምላክ) ስለሆነ፣ እኛም ሰላማውያን እና ታጋሾች መሆን ይገባናል። ካልሆነ ክርስቲያን መባላችን በተለምዶ የተገኘ ሥያሜ እንጂ መንፈሳዊ ሕይወት እና ትርጉም ሊኖረው አይችልም። ክርስቲያን ነኝ የሚል፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቀው ሰው በጥምቀት በመታሰቢያዋ ቀን እንዴት ሊረብሽ ይነሳሳል? ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው በድንጋይ እና በቦምብ ውርወራ …በግብረ ሽበራ እንዴት ይሰማራ? ታቦተ ሕጉ ላይ በሕዝቡ ላይ እንዴት ድንጋይ ይወረወራል? ይህ ከልክ ያለፈ ድፍረት እና አሳዛኝ ነገር ነው። ንቁዎች ነን፣ ምሁራን ነን፣ አዋቂዎች ነን፣ ከተሜዎች ነን እና ሥልጡን ነን በሚሉ ሰዎች መደረጉ ደግሞ ነገሩ ይበልጥ አሳዛኝ ያደርገዋል።

ጥምቀት የእምነት ምሥጢር፣ የሃይሞኖት ረቂቅነትና ምጥቀት መሠረት ያደረገ ታላቅ መታሰቢያና ባህላዊ ክቡር በዓል ነው። በዚህ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ክብረ በዓል ላይ ረበሻና ግርግር በመፍጠር ማደናቀፍ ትርጉሙ ምንድን ነው? ይህ ፀረ ሕዝብነት፣ ፀረ ሃይማኖት፣ ፀረ ሰላም እና መረጋጋት፣ ፀረ አንድነት እና በጥቅሉ የሀገር ጠላት መሆን እንጂ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም። ረበሻ እና ግርግር የሚፈጥሩ ሰዎችስ ምድን ናቸው? እነዚህም የኮሚንስት ርዝራዦች፣ እምነትና ባህልን የሚፃረሩ፣ በቁንፅል/አጉል ፍልስፍና ተነሳስተው ሃይማኖቱን የሚፃረሩ ናቸው። በተለይ ጽላቱን (ታቦቱን) የማያከብሩበት ምክንያት ታቦቱ የእግዚአብሔር ሕግ የተጻፈበት እና ማኅደረ-ቃለ እግዚአብሔር መሆኑን ስለማይቀበሉ ነው። በመሆኑም የዕንጨት ቊራጭ ወይም ድንጋይ ነው በሚል ኮሚንስታዊ አጉል እምነት ተነሳስተው <*ድንጋዩን በድንጋይ ውገር*> እያሉ እያቅራሩ ጽላቱ ላይ ድንጋይ ወረወሩበት። የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ እንደ እነዚህ በመሳሰሉት ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጐደለው ምግባረ ብልሽነትን በሚፈፅሙ ሰዎች ላይ ምን ማድረግ ይኖርበታል? መንግሥትስ ምን ማድረግ የጠበቅበታል? የሚሉ ጥያቄዎች አንስቶ መነጋገር ተገቢ መስሎ ይሰማኛል። ይህ ታላቅ ፈተና ነው። ለዲሞክራሲ የሚደረገው የትግል ጉዞ ምን ያህል ጠመዝማዛ መሆኑን ከማሳየቱ በላይ እስከ አሁን ሀገሪቱ የተጓዘችበት ጉደና ከጅምሩ ዲሞክራሲ መኖሩን እና አለመኖሩን ለመፈታተን የተሰነዘረ ነው። እንዲሁም ሕዝቡ አብሮ መኖሩና ያለመኖሩን የሚፈታተን እና ትዕግሥት አስጨራሽ በሆነ መልኩ የእምነት ነጻነቱን በማደናቀፍ የኢትዮጵያ ሕዝብን መፈታተን ማለት ነው። እነዚህ ጠላቶች መነሻቸውም መድረሻቸውም ሁሉ ምን ጊዜም ለኢትዮጵያ በጎ ነገር አይደለም። የደርግ መንግሥት እንደ ተገረሠሠ ወድያውኑ ኢትዮጵያ እንደ ሱማሊያ እና እንደ ሞንሮቢያ ትሆናለች፣ ትፈርሳለች፣ እያሉ ለኢትዮጵያ ክፉ ነገር

ሲሞኙላት እና ጥፋቷን ሲተነበዩ ነበር። ምክንያትም፡- ፩ኛ በሕዝቡ ንቀት ስላላቸው፤ ፪ኛ. እነሱ ሆን ብለው በሕዝቡ፣ በተለይ በብሔሮችና ብሔረ ሰዎች ሕዝቦች ላይ ያደረሱት በደል ስለሚያውቁ ነው። እነሱ ሥልጣን ላይ በነበሩበት ዘመን (በዘመነ ፊውዳሊዝም እና በፋሽሽት ደርግ ጊዜ) በሕዝቡ ላይ ጨቋኝ ክንዳቸውን አክብደውበት፣ ሰላም፣ እኩልነት፣ ፍትሕ እና ዕረፍት የሌለበት ኑሮ ይኖር ነበር። ኢትዮጵያ አገራችን ቂም-በቀል እሾኽ አሜከላ ዘርተውባት ስለነበር ሕዝቡ ተለያይቷል እና አብሮ አይኖርም ብለው ነበር ያ ክፉ ትንቢታቸው የተነበዩት።

አባቶቻችን ሕጉን እና ሥርዓቱን ጠብቀው፣ ባህሉን ከእምነት ጋር አጣጥመው፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ምንም ሳይቋረጥ እኛው ዘንድ ያደረሰው ባህላዊውና ሃይማኖታዊው ክብረ በዓላችን እንዴት በእኛው ዘመን ክብሩ ሊቀንስብን ይችላል? ሃይማኖታችን፣ ባህላችን እና ሰብአዊ ክብራችን እንዴት ሊደፈር ቻለ? ይህ ገና ተከባብሮ እና አብሮ መኖር የማይዋጥላቸው ኃይሎች መኖራቸውን ያመለክታል። ከዚህ መማር የሚቻለው ገና ያላለቀ የትግል ጉዞ መኖሩና ሕዝቦች መብታቸውን በእነዚህ ፀረ-ሕዝቦች እንዳይነጠቁ በተጠንቀቅ ዘብ መቆም እንዳለባቸው ነው።

አባቶቻችን ባቆዩልን እምነት፣ ልዩ ኢትዮጵያዊ ባህል እና ማኅበረ ሰብአዊ ልማድ መሠረት ታቦቶች (ጽላቶች) ከየአብያተ ክርስቲያናቱ ወደ ባሕር ሲወርድም ሆነ በቃና ዘገሊላ ዕለት ከየባሕሩ ወደ የአብያተ ክርስቲያናቱ (ወደ ጥንተ ማኅደራቸው) ሲመለሱ በሆይታ እና በዕልልታ፣ ወንዱና ሴቱ በየረድፉ ሁሉም እየዘመሩ፣ <ወረደ ወልድ፥ ወረድ ወልድ.. > እያሉ ወርደው፣ <ወወጺአ እምማይ ተርኀወ ሰማይ፥ ...መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል .,.ዘይብል ...ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር...> እያሉ ጽላቱን እያከበሩ መሸኘት በተገባቸው እንጂ ጽላቱ ላይ ድንጋዩን በድንጋይ ውገር በሚል የደንቈሮች ፍልስፍና ድንጋይ መወርወር፣ መዳፈር፣ ማዋረድ፣ የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትና መቅደሱን መሰባበር ባልተገባቸው ነበር። ይህ ታላቅ ድፍረት ከመሆኑ በላይ ሰውን የሚያስቀይም እግዚአብሔርን የሚያስቈጣ እኵይ ግብር ነው።

ይህ ሆን ተብሎ በሃይማኖታችን፣ በባህላችን፣ በሰብአዊ ክብራችን፣ በኢትዮጵያዊነት የዜግነት መብትና ዲሞክራሲያዊ የእምነት ነጻነት ላይ የተሰነዘረ ጥቃትና ንቀት ነው። ይህ ታላቅ በደል ኢትዮጵያዊ ዜጋ አደረገው ቢባል ኢትዮጵያዊ ጨዋነታችንን የሚያጕድፍ በመሆኑ ባዕድ አደረገው ቢባል ይመረጣል። ድርጊቱ ቢመረመርም ከኢትዮጵያዊ ወኔና መንፈስ ውጭ በመሆኑ፣ እውነትም የባዕድ እጅ አለበት እንጂ ከቶ ኢትዮጵያዊ እንደዚህ አያደርግም።

ይህ በክሕደትና በግብረ-ሽበራ መልኩ ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተፈፀመው ጥቃት በተመሳሳይ መልኩ በወንድሞቻችን ኢትዮጵያውያን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ክብረ-በዓል ላይ ሰላማዊ ሰልፍ በሚል (ሰይጣናዊ-ሰልፍ) ለማደናቀፍ ዝተውባቸው እንደ ነበር ይታወሳል። በዚሁ የጥፋት መንገድ እየሄዱ ሕዝቡም ሆነ መንግሥት ዝም ብሎ የሚታገሳቸው ከሆነ አደጋው ነገም በሌሎች ላይ ወይም በድጋሚ በእኛው ላይ ሊሰነዘር ይችላል። ይህ እኵይ ግብር ከወዲሁ መወገዝ ይኖርበታል። መንግሥትም እነዚህን ተከታትሎ በመያዝ ተገቢውን ቅጣት መስጠት ይጠበቅበታል። የኀብረተ ሰቡ እምነት-ሃይማኖት፣ ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት ማፍረስ፣ በግብረ ሽበራ መሰማራት እና ንብረትን ማውደም ካላስቀጣቸው፣ ሌላ ከዚህ የባሰ ምን እስኪሠሩ ድረስ ነው የሚጠበቀው? አንዳንዴ በቀጥታ ድርጊቱን የሚፈፅሙ ሰዎች ሳይሆኑ በድብቅ በሰተጀርባ ሆኖው እነሱን የሚያነሳሱ ሰዎች ናቸው ተጠያቂ የሚል ነገር ይሰማል። በእርግጥ ችግሩ ከሥሩ መድኃኒት እንዲገኝለት እነዚያም ማጋለጥና መቅጣት አስፈላጊ ነው። በቀጥታ ወንጀሉን (Crime) የሚፈፅሙ ሰዎች ደግሞ ባለማወቅ ነው ወንጌሉን የፈፀሙት ተብሎ በቸልተኝነት መታየት የለበትም። ከሕግ አኳያ ሲመረመርም አለማወቅ ራሱ ለይቅርታ (Excuse) በቂ ምክንያት አይሆንም። ለምሳሌ፡- ሰውን የገደለ ሰው ቢኖር እና መግደሉን በማስረጃ ከተረጋገጠ በኋላ ባለማወቅ ነው የገደልኩት እና ምሕረት ይደረግልኝ ቢል፣ ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም። አለማወቅ ራሱ ያስቀጣል። ስለዚህ ባለማወቅ የፈፀሙት ስለሆነ በነፃ ይለቀቁ ከተባሉ ቀጥለው ሌላ ወንጄል (Crime) እንዲፈጽሙ ፈቃድ እንደ መስጠት ይቈጠራል።

## የአጕል ፍልስፍናው <<ድንጋዩን በድንጋይ ውገር>> እና መሠረቱ፡-

ይህ ድንጋዩን በድንጋይ ውገር የሚል ጥራዝ-ነጠቅ አጕል ፍልስፍና አሁን ድንገት የተጀመረ፣ አዲስ ፍልስፍና አይደለም። መሠረቱና ፍጥረቱ ከሰይጣን ቢሆንም፣ በዘመነ ደርግ የነበሩት ኮሚንስቶች ፈፅሞ ሃይማኖት አያስፈልግም፤ እምልኮ የኋላ-ቀር አስተሳሰብ (Idealism) ሥነ-ሐሳባዊነት መሠረት ነው፤ አብያተ ክርስቲያናት የአድሃሪያን መሰብሰቢያና የጐታች ባህሎች ማእከል ስለሆኑ በሙሉ መጥፋት ወይም መዘጋት አለባቸው ብለው ያምናሉ። በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በዓይነ-ቁራኛ ይመለከታሉ።

ኮሚንስት ቀድሞውም ቢሆን ፀረ እግዚአብሔር ናቸው። እግዚአብሔር የሚለውን ቃል እንኳ ጨርሶ እንዲረሳ እግዚአብሔር ይመስገን አትበሉ፤ እንደምን ዋላችሁ ስትባሉ ወይም ስትሉ፣ እናሸንፋለን!! በሉ፤ እግዚአብሔር የሚባል

ነገር የለም፤ ፈጣሪ የለም፤ ሁሉም የተፈጥሮ (የዲያለክቲካል ማተሪያሊዝም/**Dialectical Materialism**) እድገት ግኝት ነው፣ እያሉ በግልፅ በየአደባባዩ ሲያስተምሩ ነበር። ይንንም በዘመነ ደርግ በልበ ሙሉነት በየአደባባዩ አሽባሪነትን እንደ ጀብድ በመቍጠር፣ ቀይ ቆብ ደፍተው፣ ቀይ ካባ ደርበው በትዕቢትና በማን-አህሎኝነት ሲያንጐራጕሩ የነበሩት ናቸው።

ከደርግ ወድቀት በኋላ፣ ኮሚንስቶች ኮሚንስታዊ ቀይ አርማቸውን አውልቀው፣ አንዳች ወንጀል (**Crime**) እንዳልፈፀሙ ታራ ሰው መስለው፣ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ሰርገው በመግባት፣ ለትንሽ ጊዜ አድፍጠው ተቀምጠው ነበር። ነገር ግን እንደ አዲስ አሁን ያ የተለመደው ግብረ ሽበራ እና ፀረ ሃይማኖት ተልእኳቸው እንሆ በመፈፀም ላይ ይገኛሉ። እውነቱ ይህ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ይህነን መጥፎና አሳፋሪ ድርጊት በዝምታ ያልፈዋል? በተቀናጀ መልኩ ሕዝብና መንግሥት ተባብረው ይህንን የሀገራችን መጥፎ ገጽታ ሊለውጡት ይገባቸዋል።

ድንጋዩን በድንጋይ ውገር እያልክ ጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያ ለማፍረስ መሞከር፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ወግና ሥርዓትን ማበላሸት፣ የሕዝቡ ማኅበራዊ ሕይወት ማዛባት፣ ሰላምና ዕረፍት መንሳት፣ በድንጋይ ውረወራ የሕዝቡ ሕይወት አደጋ ላይ መጣል፣ እና እነዚህ ሁሉ የሥልጡን ሕዝቦች ሥራ አይደለም። እንዲያውም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ድንጋይ መወርወር ማለት ድንጋይ ራሱ፣ ያልሰለጠነ፣ ኋላ-ቀር መሆን ማለት ነው እንጂ ምንጊዜም ቢሆን የሥልጣኔ ምልክት አይሆንም፤ ሆኖም አያውቅም። ይህ በአርአያ እግዚአብሔር ከተፈጠረ ከሰብአዊ አስተሳሰብ ውጭ እና ያልሰለጠነ የበረሃው እንስሳ (**wild Animal**) መሆን ማለት ነው። ሰዎች ናቸው ከተባለም ደግሞ ሰዎቹ የነውር፣ የመርገም እና የኃጢአት ድብልቅ ያደፈረሳቸው የመርገም ትውልድ ፍሬዎች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ትውልደ-መርገም የሀገራችን ጥንታዊነትን፣ አኩሪ ታሪክን፣ ብሔራዊ ክብርን እና ነፃነትን የሚያጐድፉ፣ የገዛ ሀገራቸውን ሕግ በመተላለፍ ክብሯን የሚገፉ የተረገሙ ጠፊ ተውልድ ተብለው ነው መታወቅ ያለባቸው። መንግሥትና ሕዝብ ከወዲሁ ብዙ ብልሽት ሳያስከትሉ ይህ የሕግ መተላለፍ ወንጀል (**Crime**) በፈፀሙት ውሉደ-መርገም ላይ እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፤ ጊዜ ሊሰጣቸውም አይገባም።

በመንግሥት በኩል አስፈላጊው እርምጃ ስላልተወሰደባቸው እነዚህ ሕግ አልቦ ሰዎች ሕግን በመተላለፍ በሰዎች ሕይወት ሲቀልዱና የዜጎች ሰብአዊ ክብርን፣ የእምነት ነፃነትን እና የዲሞክራሲ መብቶችን ሲገፉ ይታያሉ። ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው ደግሞ በሰላምና ፀጥታ አስከባሪ በፖሊስ ሠራዊትም ላይ ሳይቀር ድንጋይ እየወረወሩ ጉዳት ሲያደርሱ፣ ሲያቈስሉ እና ሲገድሉ መታየቱ ምንያህል ሕግን የማያከብሩ ወንጌለኞች እንደሆኑ ያመለክታል።

በተገላቢጦሽ "ወርቅ ላበደረ ጠጠር" እንደሚባለው ካልሆነ በስተቀር፣ ሰላምን በማስከበር ተልእኮ ተሰማርተው አገርን እና ሕዝብን በማገልገል የሚገኙ ወንድሞቻችን የፖሊስ አባላት እና የፀጥታ አስከባሪ ወገኖቻችን በተለይ ግፍ ሊፈፀምባቸው አይገባም። የዜግነት መብታቸው፣ ሰብአዊ ክብራቸው፣ ሕይወታቸው እና ንብረታቸው ሁሉ እንደ ማንኛው ኤትዮጵያዊ ዜጋ ሊከብርላቸው ይገባል። እንዲያውም ለሚያበረክቱት አገልግሎትና መስዋዕት ልዩ ክብር፣ ምስጋና እና ሽልማት በተገባቸው እንጂ ድንጋይና ቦምብ ሊወረውርባቸው ባልተገባ ነበር። ይህ ከስልጣኔ እና ከሰብአዊነት እኳያም ሆነ ከዲሞክራሲያዊ የዜግነት መብት አኳያ ሲታይ የተፈፀመባቸው በደል አግባብ የለውም። እነሱ ግን ክብር ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም ጥይት የጐረሰው ብረት ታጥቀው እያሉ ወንድሞቻችንን፣ ሕዝባችንን በታጠቅነው ጠመንጃ አንገድልም፤ ይግደሉን እንጂ በሚል ቈራጥነትና ትዕግሥት ድንጋይ ሲወረውርባቸው እና ሲገደሉ ዝም ማለታቸው በጣም የሚያስደንቅ ትዕግሥት ነው። ይህ ዓይነቱ ትዕግሥትም የትም ሀገር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ለምሳሌ በአመሪካ በ(**United States of America**) በፖሊስ ላይ ድንጋይ መወርወር በቀረ እና ፖሊስ ድንገት አቁሞ ሲጠይቅም ሆነ ሲፈትሽ መጨቃጨቅ አይፈቀድም። ፖሊሱን ያቆምከኝ ወይም የፈተሽከኝ ምንም ሳልበድል ነውና ፍተሻህ አግባብ የለውም እያልክ በቦታው ፖሊሱን መነጋገር ክልክል ነው። እንዲያውም በሚጨቀጭቀው ሰው ላይ ፖሊሱ ራሱ አስፈላጊ መስሎ የታየውን የኃይል እርምጃ እስከ መውሰድ የሚያስችለው መብትና ነፃነት አለው። ነዘነዘኝ (**Harassed me**) ብሎ ቅጣት ሊሰጥ ይችላል። ፖሊስ በድሎኛል ማለት የሚቻለው በፍርድ ቤት ሄዶ የደረሰውን በደል በዳኛ ፊት በመከራከር ብቻ ነው። ምንም ቢሆን ከፖሊስ ጋር ጭቅጭቅና እንካ-ስላንቲያ መግጠም ከሥርዓቱ በኩልም ሆነ የምን አልባሽ ፕሊሱ ሊወስደ ከሚችል የኃይል እርምጃ ለመቀነስ ሲባል፣ ‹**Yes Sir**› እና ‹‹**Yes Officer**›› እያልክ መታዘዝ ነው እንጂ በሀገራችን እንደ ሚደረገው አይደረግም። ስልጡን በሚባሉ አገሮች ሁሉ ሕዝቦች የገዛ ሕጋቸውን አያፈርሱም፤ በፖሊስ ላይ፣ በሕዝብ ላይ፣ በማንም ላይ ድንጋይን ወይም ቦምብን አይወረውሩም፤ ይህ ነውር ነው።

ከዚህ አኳያ ሲታይ፣ በኢትዮጵያ እየታየ ያለው ነገር ከመጠን ባላይ አስደናቂ ነው። ፖሊስ ወይም ዘብ የቆመው የሕግ/ፀጥታ አስከባሪ ኃይል(ሰው) ሰላምና ፀጥታን ለማስከበር ጥይት የጐረሰ ብረት (ማሳሪያ) አንግቦ ሲያበቃ

የገዛ ራሱ ስላሙንና ሕይወቱን (ድኅንነቱን) ማስከበር ካልቻለ የሀገሪቱን (የሕዝቡን) ሰላም ሊያስከብር አይችልም። በጣም! ይገርማል! ያስገርማልም። ረብሸኞች አጐንብሰው ድንጋይ አንስተው ግንባሩ ላይ እስኪ ፈነክቱት እና ቦምብ ሲያፈነዱበት ፖሊስ ዝምብሎ እስከ ሞት ድረስ መታገሥ እና መሞት ምን ማለት ነው? ይህ እንደ በግ በአርምሞ ዝም ብሎ መታረድ እና መሞት ረብሸኞቹ ትዕግሥት ብለው አይጠሩትም፤ እንዲያውም አጉል መስዋዕት በማለት ሳያጣጥሉት አይቀሩም። እንደ ዚህ እስከ ሞት መታገሥም የትም አገር ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም። አረ በኢትዮጵያ አምላክ! ሕግ ይኑር፣ ሕግ ይከበር፣ የሕግ የበላይነትም ይረጋገጥ። እንዲህ ማለት ደግሞ በዘመነ ደርግ ይደረግ እንደነበርው፣ ፖሊስ/ወታደር ከሕግ ውጭ ሰውን እንደ ፈለገ ይግደል ማለት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት።

በየትም ሀገር እንደሚሠራው ሁሉ በቅድሚያ ፀጥታ አስከባሪው (ፖሊስ) በሥራው ተሰማርቶ ሲሠራ ሊደርስበት የሚችል አደጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ሕይወቱን እና የዜግነት መብቱን ሊያስከብርለት የሚችል ሕግ ሊኖር ይገባል። በቅድሚያ ሕይወቱን ለመጠበቅ፣ ለመከላከልና እርምጃ እስከ መውሰድ የሚያስችለው በሕገ የተደገፈ ሙሉ ኃይል (**Enforcement**) ሊሰጠው ይገባል። ዓመፅና ግብረ ሽበራም በዚህ መልኩ ነው መቆጣጠር የሚቻለው ብየ አምናለሁ።

ሕግን በመተላለፍ አጐንብሶ ድንጋይም ሆነ ሌላ አደገኛ ማሳርያ (**Deadly Weapons**) የሚያነሳ ማንኛውም አደጋ ጣዩ ሰው ድንጋዩን ወይም ማሳሪያውን ከማንሳቱ አስቀድሞ (ቀድሞ) ፖሊሱ አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ አለበት። ካልሆነ ፖሊስ በድንጋይ ተገደለ ማለት በሀገሩ ፖሊስ የለም፣ ሕግ አልተከበረም፣ ሰላም ማስከበርም አልተቻለምና የፖሊስ ኃይል (**Enforcement**) ደካማ ነው የሚል መልእክት ነው የሚያስተላልፈው።

---

*<<ሀገር የጋራ ነው፣ ሃይማኖት የግል ነው>>* አሉ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ እየተባለ ይነገራል። ትክክለኛ አባባል ነው።
ምክንያቱም፡-

*ኢትዮጵያዊ ማለት ከተሜ ወይ አዲስ አበባዊ ብቻ አይደለም፤*
*ኢትዮጵያዊ ማለት የአንድ ብሔር ሕዝብ ብቻ አይደለም፤*
*ኢትዮጵያዊ ማለት ምሁሩ ብቻም አይደለም።*
*ኢትዮጵያዊ ማለት ሃብታሙ እና የደላው ብቻ አይደለም።*
*ኢትዮጵያዊ ማለት ወንዱ ብቻም አይደለም፤*

*ወንዱ፣ ሴቱ፣*
*ሽማግሌ፣ አዛውንቱ፣*
*ህፃናቱ፣ ወጣቱ፣*
*ወደድንም ጠላንም፣ ኢትዮጵያዊያን ናቸው እንደ ጥንቱ።*

*ኢትዮጵያዊ ማለት ፖለቲከኛው ብቻ አይደለም፤*
*አገር የጋራ ነው፤*
*ዜጎች ሁሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው።*
*የአንዱን እምነት ሌላው ሊያረክሰው፤*
*የአንዱን መብት ሌላው ሰው ሊጥሰው፤*
*አይገባም፣ ይህ ነውር ነው።*

*አብሮ መኖር፣ መተባበር፤*
*መደጋገፍ፣ ይገባል መከባበር፤*

*የከተሜ፣ የምሁሩ ድምፅ ሲሰማ ሲቆጠር፤*
*የገበሬው፣ የገጠሬው፣*
*የሕዝብ ድምፅ ሊሻር፤*
*አይገባውም መሸርሸር።*

*በኢትዮጵያዊነት የጋራ እምነት፤*
*አራሹ፣ አምራቹ፣ ነጋዴው፣*

*የቢሮ ሠራተኛው፣ የፋብሪ ሠራተኛው፤*
*የቤት ሠራተኛው ሁሉ፡ …ሁሉም፡ ..በሙሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው።*

*በመጥፎ ግብር ብግብረ ሸበራ፤*
*በአድማ በድንጋይ ውርወራ፤*
*የትም አልታየም ሀገር ስትለማ-ስትሠራ፤*

*በአራት ኪሎ በመርካቶ፤*
*ቦምብና እና ድንጋይ ዘርቶ፤*
*ተባለና አገር ለምቶ፤*
*የሀገር ግንባታ ባሕረ-ሐሳብ ተገብቶ፤*
*ነገር ግን፣ …ሰላማዊ ትግል ዋናው ተረስቶ፤*
*የሕዝቦች ቁጣ ማዕበል ተነስቶ፤*
*የአንዱ መብት ሲከበር የሌላው …ቀርቶ፤*
*ይህማ አይሆንም፣ …. አያዋጣም ከቶ፤*
*ውኃ መሆን ነው፣ በውኃ ተበልቶ።*

*……………………………………*

*በተመሳሳይ ርዕስ ወይም በሌላ እስክንገናኝ ድረስ ድኅና ሰንብቱ።*

---